# ቀስተ ደመና ሬድዮ

## ትችት

01/11/02

# የቡና ቀውስና የቡና ወሬ

በአለም ደረጃም ሆነ በሀገራችን ከአራት አመታት ጀምሮ በአለም የቡና ገበያ በተከሰተው የዋጋ ማሽቆልቆል ምክንያት ስለደረሰው ቀውስ ብዙ ተተችቷል። የደረሰው ኪሳራ ይህ ነው አይባልም። ከዛሬ አመት ዋጋ ጋር ሲነፃፀር የቡና ዋጋ ቢያንስ በሃምሳ በመቶ ወድቋዋል። በዚህ አመት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የላከችው ቡና በብዛቱ ባለፈው አመት ከላከችው ይበልጣል። ከዚህ ሽያጭ ያገኘችው ገንዘብ ግን በመቶ አስር ሚልዮን ዶላር ቀንሷል። ከአንድ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ የቡና አምራች ገበሬዎች እንኳዋን ማትረፍ ቀርቶ ቡናውን ለማምረት ያወጡትን ወጭ ሆነ የተበደሩትን ገንዘብ መሸፈንና መክፈል ስላልቻሉ በእዳ ተዘፍቀው ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀው ይገኛሉ።

ጉዳዩ በአለም ደረጃ ከስልሳ ሚልዮን በላይ የገበሬ ቤተሰቦችን ህልውና አደጋ ላይ የጣለ ከባድ ቀውስ ነው። ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ይህንን ቀዉስ በማስመልከት ኦክስፋም የተባለው አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅት እነዚህ ገበሬዎች ከወደቁበት ቀውስ እንዲወጡ ውትወታ ለማድረግ አንድ ዘመቻ ጀምሩዋል። ስለ ችግሩ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በአዲስ አበባ አንድ ስብሰባ ተካሂዷል። በዚህ መለስ ዜናዊም በተገኙበት ስብሰባ ላይ ቀውሱ ከየትና ለምን እንደመጣ ሁሉም የየበኩሉን አስተያየቱን ሰጥቱዋል። በትናንሽ ቡና አምራች ገበሬዎች ላይ በመፈፀም ላይ ስላለው ግፍም ብዙ አሀዞች በመለስ ዜናዊ ሳይቀር ተደርድረዋል።

ተብለው ተብለው ካለቀላቸው አንዳንድ እውነታዎች ተነስተን ነገሩን እንመልከት። አቶ መለስ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች የደቡብ አገሮች ለሚደርሱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶቸ አለም አቀፉን ስርአት ተጠያቂ ማድረግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያዘወተሩ መጥተዋል። ከዚህ ቀደም በአንድ ስብሰባ ላይ የበለፀጉ አገሮች በአንድ በኩል የድሃ አገሮች የእርሻ ምርቶች በሰሜን አገር ገበያዎች ዝር እንዳይሉ እያከላከሉ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ገበያችንን በርግደን እንድንከፍት እያስገደዱ ናቸው ብለው ወንጅለዋቸዋል። በማያያዝም የበለፀጉት አገሮች ከዚህ አልፈው ተርፈው ለገበሬዎቻቸው ድጎማ እያደረጉ ምርቶቻቸውን በድሆች አገሮች ገበያ ላይ በአልባሌ ዋጋ በማፍሰስ እንዴት የደቡብ አገሮችን ገበሬዎችና የግብርናውን የኢኮኖሚ ዘርፍ በማቆርቆዝ ላይ እንዳሉ አጋልጠዋል። ነገሩንም ጠቅለል አርገው ሲያቀርቡ ዛሬ በአለም ደረጃ የተተከለው የንግድ አሰራር ለበለፀጉት እንጂ ለድሃ አገሮች እንዳልተበጀ ከዚህ የተሻለ ማስረጃ የለም ሲሉ ሁሉ ተደምጠው ነበር።

በዚህ በቡናው ቀውስም ጉዳይ ከዚህ የተለየ አስተያየት የላቸውም። በስብሰባው ተገኝተው ባደረጉት ንግግር በመፈፀም ላይ ስላለው ግፍ በተጨባጭ ሲያስረዱ ኪሎ ግራም ቡና የበለፀጉት አገሮች ሲደርስ 220 ብር ቢሸጥም ዛሬ ከዚህ ኪሎ ቡና ሽያጭ የሃገራችን ገበሬ የምትደርሰው እናቷም አባቷም ሰማንያ አምስት ሳንቲም እንደሆነና የዛሬ አምስት አመት ገበሬው ከዚህ ሽያጭ ስድስት እጥፍ ያገኝ ነበር በማለት የሁኔታውን ግፈኝነት ጠቁመዋል።

የአለምን የቡና ገበያ የሚቆጣሩት አራቱ ግዙፍ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ደግሞ ከድሃ አምራች ገበሬዎች ቡና የሚገዙበት ዋጋ ከአመት አመት እያሽቆለቆለ ቢሄድም በበለፀጉት አገሮች ላለው ሸማች ምንም ቅናሽ ስለማያደርጉ የሚያገኙት ትርፍ የዚያኑ ያህል ወደላይ እያሻቀበ መጥቷል። ባለፈው አመት የድንበር ዘለሉ ኔስሌ ኩባንያ ዋና ስራ አስኪያጅ ስለአመቱ የስራ ውጤት ሪፖርት ሲያቀርቡ *" ባያዝነው አመት በአለም የቡና ገበያ ላይ የተከሰተው ሁኔታ አመቺ ስለነበረ የኩባንያው ትርፍ ከፍተኛ እድገት አሳይቱዋል "* በማለት ያደረጉት ንግግር የዚህ የተዛባ ሁኔታ ነፀ ብራቅ ነው።

ወደ አቶ መለስ ንግግርና የመፍትሄ ሃሳብ ከመመለሳችን በፊት ስለቀውሱ መሰረታዊ ምክንያቶች አንዳንድ ነጥቦችን እናስቀምጥ። በዚያውም ግፈኛና ለድሆች አገሮች ያልተመቻቸ ብለው አቶ መለስ የተቹት ስርአት ለቀውሱ

ዘለል ኩባንያዎች ናቸው። የቡና ዋጋ የሚተመነው ያው በነፃ ገበያ መርህዎች መሰረት በገበያ የሚቀርበው ወይም ሊቀርብ የሚችለው ምርት ካለው የቡና ፍላጎት ጋር እየተነፃፀረ ነው። በገበያ ላይ የሚቀርበው ቡና ከሚፈለገው በላይ ከተትረፈረፈ ዋጋ ያሽቆለቁላል። በሆነ ምክንያት ገበያ የሚቀርበው ቡና የሚፈለገውን ያህል ካልሆነ ደግሞ ዋጋ ይወጣል። ሰፕላይና ዲማንድ የሚሉት ቀላል የገበያ ሎጂክ መሆኑ ነው።

በአሁኑ ወቅት በድንበር ዘለል ኩባንያዎቹም ሆነ በነሱ ዙሪያ በሚሽከረከሩ ኤክስፐርቶች የቀውሱ ዋና ምክንያት ተብሎ የሚቀርበው ይሄው የነፃ ገበያ ሎጂክ ነዉ። ያለው የቡና አቅርቦት ከሚፈለገው በላይ ስምንት በመቶ ትርፍ ነዉ። ለምን እንደዚህ ተትረፈረፈ ሲባል ደግሞ ተደጋግሞ የሚነሳው የቪየትናም ስም ነው። ባለፉት አስር አመታት ቪየትናም ከየት መጣች ሳይባል በአለም የቡና ገበያ ቁልፍ ተዋንያን ሆናች። እየወጣች እየወጣች ሄዳ ከብራዚልና ከኮሎምብያ ቀጥላ ሶስተኛ ቦታ ይዛ የነበረችው አሁን ኮሎምብያን ቀድማ ' 'ሮቡስታ' ለተባለው ዝቅተኛ ደረጃ ቡና ሁለተኛውን ቦታ ይዛለች። ነገር ግን አንዳንዶች ለማስመሰል እንደሚፈልጉት በአለም ደረጃ ለደረሰው ቀውስ ቪየትናምን ተጠያቂ በማድረግ ጥያቄውን መሸንት አይቻልም። መሰረታዊ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶችም አሉ

መጀመሪያ የሚነሳዉ ጥያቄ ቡና ከቁጥጥር ዉጭ በሆነ መልክ ለምን በገፍ ገበያ ላይ ፈሰሰ? የሚለው ጥያቄ ነዉ። እንደሚታወቀዉ የዘይት አምራች አገሮች ገበያ ላይ የሚያወጡትን ቤንዚን (በዚያውም ደግሞ በአለም ገበያ የቤንዚንን ዋጋ) የሚቆጣጠሩበት ኦፔክ ወይም ኦርጋናይዜሽን ኦፍ ፔትሮልየም ክስፖርቲንግ ካንትሪስ የሚባል ድርጅት አላቸዉ። ቡና ላኪ አገሮችም በዚሁ መልክ እየመከሩና ኮታ እየተሙኑ ገበያ የሚያቀርቡትን ቡና የሚቆጣጠሩበት አለም አቀፍ የቡና ስምምነት ወይም ኢንተርናሽናል ኮፊ አግሪሜንት የሚባል የጋራ ድርጅት ነበራቸዉ። ይህ ድርጅት በ1954 እ.ም. ተቋቁቁሞ ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ በስነስርአት ሲሰራ ቆይቶ ነበር። ከግሎባላይዜሽን ስርአት ማንሰራራት ጋር ተያይዞና በአለም ደረጃ የነፃ ገበያ መርህዎች በተግባር መዋል አለባቸው በሚል ድንበር ዘለል ኩባንያዎቹ በአሪካን መንግስት ታግዘው ባደረጉት ግፊትና ጫና ይህ ቁልፍ የሆነ የቡና ዋጋ መቆጣጠሪያ ድርጅት በ1982 እ.ም. እንዲፈርስ ተደረገ።

ሁለተኛው ጥያቄ የቡና አምራች አገሮች ይህንን ግፊት ተቋቁቁመው ለምን የቡናን አቅርቦትና ዋጋ ለመቆጣጠር አይሞክሩም የሚለው ጥያቄ ነው። ተሞክሩዋል። ለምሳሌ የቡና አምራች አገሮች ማህበር (ወይም አሶስየሽን ኦፍ ኮፊ ፕሮዱሲንግ ካንትሪስ) የሚባለው ድርጅት ተቋቁቁሞ ይህንን የመቆጣጠር ተግባር ለማከናወን ሞክሮ ነበር። ይህ ማህበር ለምሳሌ ግንቦት 9 ቀን 1993 እ.ም. ቡና አምራች አገሮች ከምርታቸዉ 20 በመቶዉን ገበያ ከማውጣት እንዲቆጠቡ ዉሳኔ አሳልፎ ነበር። ይህ ውሳኔ ለስድስት ወር ያህል ከተከበረ በሁዋላ መፍረክረክ ጀመረ። ማህበሩም የሚያዳምጠኝ ከሌለ ምን ዋጋ አለዉ በሚለው ቅሬታው ላይ የድንበር ዘለል ኩባንያዎቹን ግፊት መቋቋቁዋም ስላቃተዉ እሱም በተራው መስከረም 20 ቀን 1994 እ.ም. ስራውን አቆመ። ለታየዉ ድክመት ሁለት ምክንያቶች አሉ።

አንደኛ በተለይ ድሆች የሆኑት የአምራች አገሮች ገበሬዎች አስከፊ አዙሪት ዉስጥ መዉደቃቸው ነው። ዋጋ እየወደቀ ሲሄድ በዚያው ልክ ገቢያቸዉ እየወደቀና በተለይ ምንም ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ ከባንኮችም ሆነ ከሌሎች ተቋማት የተበደሩትን ለመመለስ ባወጣው ያውጣው እያሉ ያላቸውን ሁሉ ገበያ ማቅረብ ተገደዱ። ይህ ደግሞ የቡናን ዋጋ ይበልጡኑ እያሽቆለቆለዉ ሄደ። አስከፊ አዙሪት ያልነዉ በዚህ መልክ ሲያመቻቸዉ ብቻ ለነፃ ገበያ መርህዎች እንገዛለን የሚሉት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ድሆችን እያፎካከሩ ሰማይ ጠቀስ ትርፍ በመዛቃቸዉ ብቻ አይደለም። ለይበልጥ ድህነት እየተዳረግን ያለንበት ሌላዉ ምክንያት ራሱ ድህነታችን በመሆኑ ነዉ።

ሁለተኛ ይህ ባወጣ ያውጣው የተቻለዉን ገበያ እናውጣ የሚለዉ ግፊት የሚመጣዉ ከድሃ አምራቾች በኩል ብቻ አይደም። መንግስታትም ቢሆኑ ይህንን ግፊት ያደርጋሉ። ከኮሎንያሊዝም ወቅት አንስቶ ድሆች አገሮች በአለም ኢኮኖሚ የተወሰነባቸው ድርሻ አንድ ወይም ሁለት ሸቀጦችን ገዥወች ራሳቸው በሚተምኑት ዋጋ ለአለም ገበያ የማቅረብ ሚና ነው። እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገሮች በየአመቱ ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ ሴሌሳ በመቶ ያህሉ የሚገኘዉ ቡና በመላክ ነው። ዋጋ እየወደቀ ሲሄድ ብዙ ለመሸጥ የሚገደዱት የገቢን መጠን እንጠብቃለን ከሚል ተስፋ ተነስተው ብቻ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ዛሬ ሁሉም እያማረረበት ያለው የነአለም ባንክና የነአይኤም ኤፍ አጥፊ ተፅእኖ አለ። እነዚህ ለድሆች አገሮች ዘላቂ ልማት (ሰስቴይንኤብል ዲቨሎፕሜንት) ፀር የሆኑ አጥፊ ተቋማት

ከባርያ ንግድ ዘመን አንስታችሁ ስታደርጉ እንደነበረው አሁንም በኤክስፖርት ላይ ያተኮረ የእድገት ጎዳና ያዙ እያሉ በማስገደድ ብቻ አያቆሙም። ያላችሁን ምርት ባወጣው ዋጋ ገበያ እያወጣችሁ ሽጡና በየአመቱ የሚጠበቅባችሁን ብድር ክፈሉ እያሉ ድሆች አገሮችን አስጨንቀው ይይዛሉ።

በሃገራችን በቡና አምራቾች ላይ የደረሰው ከፍተኛ ቀውስ በዚህ መልክ ከተጫነብን የማያዋጣ የእድገት አቅጣጫ፣ አገራዊ ራእይ አልባ በመሆናችን ከተንበረከክንለት የግሎባላይዜሽን ስርአት፣ ለበለፀጉት አገሮች ጥቅም እስከሰራ ድረስ ብቻ በተግባር ከሚውለው 'የነፃ ገበያ' ኢኮኖሚ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ከባድና አጠቃላይ ቀውስ ነው። ይህንን ግልፅ እውነታ ተቀብሎ ለሃገራችን አጠቃላይ ቀውስ አጠቃላይና ሁለገብ መፍትሄ መሻት ያስፈልጋል። እነ አቶ መለስ በእንዲህ አይነቱ ሂደት ለመሰማራት የተሰናዱ አይመስልም። ከፍ ብለን በጠቀስነው በቡናው ቀውስ ጉዳይ በተጠራው ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ላይ ' ግፉ ሞልቶ እየፈሰ ነው፣ እንተዛዘን፣ ለቡናችን ተገቢ ዋጋውን ክፈሉን' ብለው የግዙፎቹን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ተወካዮች ሲማጠኑ ተደምጠዋል። ከዚህ አልፈው ግን እነዚህ ሃይሎች እንዲህ እንዲናጥጡና በድሃ ደምና እንባ እንዲነግዱ ያስቻላቸውን አለም አቀፋዊ ስርአት እንኳዋን ሲያወግዙና በቅጡ ሲወርፉም አልተደመጡም። ያንፀባረቁት ተንበርካክ ሊባል የሚችል አቋዋም ነው። ያሉት ምንድን ነው?

"'ማንም ራሱን ማታለል አይገባውም። ግሎባላይዜሽን ያለና ገና የሚኖር ክስተት ነው።" ንግግራቸው በእንግሊዝኛ ስለነበረ ቃል በቃል ብንጠቅሳቸው አባባላቸው 'ግሎባላይዜሽን ኢዝ ሂር ቱ ስተይ' የሚል ነበር። ይህ የዚህ ስርአት አራማጆች የተለቀቁበት ተራ ማወናበጃ ነው። ምንም ማድረግ አይቻልም ከነ ግፉ ከነ ጥፋቱ እንንበርከክለት የሚል ትጥቅ አስፈቺ መልእክት ነው።

በሶስት ነጥቦች ሃሳባችንን እንቋዋጥር። አንደኛ ግሎባላይዜሽን ያለና የሚኖር ክስተት መሆኑን ማንም አይክድም። የተባለው ዛሬ ያለው ግሎባላይዜሽን ለጥቂት ግዙፍ ድንበር ኩባንያዎችና ስድ የሆነው የነፃ ገበያ ግርግር ለተመቻቸው ጥቂት ተጠቃሚዎች እንጅ ሰማንያ በመቶ ለሚሆነው የአለም ህዝብ አይሰራም ነው የተባለዉ። በዚሁ ጉዳይ ምክትል ዳይክተር ከነበሩበት ከአለም ባንክ ስራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት የኢኮኖሚ ኖቤል ተሸላሚ ጆሴፍ ስቲግሊትዝ በትክክል እንዳስቀመጡት ነው። "ያለው ግሎባላይዜሽን ለአለም ድሆች አይሰራም። ለአለም አካባቢ ጥበቃ አይሰራም። ለአለም የተረጋጋ ኢኮኖሚ አይሰራም።" ሁለተኛ ነጥብ ዛሬ በአለም እያየለ የመጣው ፀረ ግሎባላይዜሽን እንቅስቃሴ የአለምን በኢኮኖሚ መተሳሰርና መቀራረብ የሚቃወም እንቅስቃሴ ሳይሆን በግልፅ " ለሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን" ብሎ የሚንቀሳቀስ የማይበገር አለም አቀፋዊ ሃይል ነው። ሶስተኛ ይህንን ሃቅ ሳይገነዘቡና ለፍትህና ለልማት ሲባል ከዚህ ለሌላ አይነት ግሎባላይዜሽን የሚደረገው ትግል ህዝብን አሰልፎ እስካልተደባለቀ ድረስ ስለ ስርአቱ ግፈኛት ስታቲስትክስ መደርደርና ስለ ቡናው ቀውስ አስከፊነት መተረክ ከቡና ወሬ የማያልፍ ዲስኩር ነው እንላለን።